# ምርጫ በህወሓት/ኢህአዴግ ስር
(ከመፅሐፍ የተቀነጨበ)

የውብማር አስፋው (የአቶ ገብሩ አስራት ባለቤት) በ2001 ዓ/ም "ፎኒክስዋ ሞታም ትነሣለች፣ ያልተቋጨው የትግራይ ሴቶች ገድል" በሚል ርእስ በፃፈችው መፅሓፍ በህወሓት "ምርጫ" ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ሊያሳይ የሚችል ተጨባጭ ምሳሌ በገፅ 175 ላይ እንደሚከተለው ፅፋለች፡፡

"የህወሓት አመራር ባስቀመጠው መመሪያ መሰረትም ማህበሩ በሁለተኛ ጉባኤ የሚሳተፉትን ሴቶች ምርጫ አካሄደ፡፡ ጉባኤውም በመቀሌ ማዘጋጃ ቤት አዳራሽ በጥቅምት 1988 ዓ/ም ተሰየመ፡፡ እንደተለመደው ያለፈው የማህበሩ እንቅስቃሴ ከተገመገመ በሁዋላ የማህበሩ መርሃ ግብርና ህገ ደንብ ፀደቀ፡፡ የማህበሩ አመራር ምርጫ ከመካሄዱ በፊት ግን የቆዩትን ነባር የማህበሩ አመራርና የተወሰኑ ለአዲሱ አመራር እንዲመረጡ የተፈለጉትን ታጋዮች የሚያሳትፍ በአንድ የፖሊት ቢሮ አባል የሚመራ ስብሰባ ተካሄደ፡፡

የስብሰባው አላማ ፖሊት ቢሮው የማህበሩ አመራር እነማን እንደሚሆኑና የሊቀ መንበርነቱን ቦታ ማን መያዝ እንዳለባት የወሰነውን ውሳኔ ማሳወቅና ውሳኔው ተግባራዊ ስለሚሆንበት መንገድ መመሪያ መስጠት ነበር፡፡ በዚህ መሰረትም ከታጋዮች ማኸል እነማን የማህበሩ አመራር ሊሆኑ እንደተመደቡ ተገለፀ፡፡

ለአዲሱ አመራር አስቀድመው ከተመለመሉት መካከል የማስታውሳቸው፣ አኸዛ ብርሃነ (ጣንጡ)፣ ሓዳሽ አለሙ፣ ቅዱሳን ነጋ፣ ሰንደል አደም፣ ፀሃይቱ ባህታ፣ ትርፉ ኪዳነማርያም ሲሆኑ ሊቀ መንበሯም ቅዱሳን ነጋ እንደምትሆን ተገለፀ፡፡"

የውብማር እንደምትገልፀው ፖሊት ቢሮው (እነ ገብሩም የነበሩበት) ስብሰባውን የሚመሩ፣ እጮዎችን የሚጠቁሙና በእጩነት የሚቀርቡ ስለመደበ፤ ለ "ምርጫ" ጥቆማ ሲጀመር ስብሰባውን የሚመሩት እጃቸውን ከሚያወጡት ተሳታፊዎች ለእነማን እድል መስጠት እንዳለባቸው፣ እድል የሚሰጣቸው እነማንን መጠቆም እንዳለባቸው፣ የሚጠቆሙትም በእነማን እንደሚጠቆሙ አስቀድመው ያውቁ ነበር ማለት ነው፡፡

በዚህ መሰረት ጉባኤው እንደ ጉባኤ ትርጉም የለውም፤ ምስጢሩን ለማያውቁ ማታለያ ትያትር ነው፡፡ ይህ በድርጅቱ አባሎች ውስጥም ነፃ ምርጫ የማይፈቅደው ፀረ ዴሞክራሲ ቡድን እንደ ጠላቶች ከሚያጥላላቸው ተቃዋሚ ሃይሎች ጋር እንዴት ሳያስፈራራ፣ ሳይሰርቅ ሳያጭበረብርና ጉልበት ሳይጠቀም ከስልጣን ሊወገድበት የሚችል ነፃ ምርጫ እንዲካሄድ ሊፈቅድ ይችላል?

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views.
(የኢትዮጵያ ጠላት የትግራይ ወዳጅ ሊሆን ከቶ አይችልም)